ICARDA
Science for resilient livelihoods in dry areas

# Strategic recommendations for livestock market development in Ethiopia

*Policy brief submitted to the State Minister Office, Ministry of Agriculture, Addis Ababa, Ethiopia*

Girma T. Kassie[1], Aynalem Haile[1], Kelifa Hussien[2], Yoseph Mekasha[3], Getachew Legesse[4], Asrate Tera[5]

[1]International Center for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA), Addis Ababa, Ethiopia. [2]FRIGORIFICO Boran Foods PLC/Allana Group, Addis Ababa Ethiopia. [3]Agricultural Transformation Agency, Addis Ababa, Ethiopia. [4]International Livestock Research Institute (ILRI). [5]National Animal Genetic Improvement Institute (NAGII), Addis Ababa, Ethiopia.

November 2021

## Summary

This note summarizes the key recommendations for livestock market development we are making based on the scientific evidence generated by ICARDA and its partners over the last decade. This note is to be submitted to the State Minister, Ministry of Agriculture, and is written in Amharic. The English summary will only highlight the key problems of and strategies for the development of livestock marketing in Ethiopia. Ethiopia is endowed with immense and growing livestock population. This resource is the mainstay of livelihood of millions of rural Ethiopians and is a key pillar of the country's agrarian economy. Basic indicators show however that the productivity of the livestock sector is very low and, hence, the country is hardly benefiting as much as it should from this huge resource. Smallholder farmers are the main custodians of the livestock population and the main purpose of livestock keeping is not necessarily profit making. Rather the key purposes are providing farm labor, cash income, food and drinks, insurance against agricultural risk, and social privilege. The fact that livestock production is not market oriented has a significant impact on our domestic and international livestock marketing. The challenges of livestock marketing are numerous and interwoven. We annotate the key challenges and the strategic recommendations we make as follows.

The challenges are:

i. The market supply of livestock is very erratic and disconnected from market signals.

ii. There is limited access to roads as rural road development efforts barely take into consideration improvement of livestock marketing or agricultural marketing in general. Farmers have limited access to bigger and more rewarding markets while exposing their animals and themselves to arduous trekking every week.

iii. The livestock markets are usually marginal plots of land with no fences, water troughs, feedlots, veterinary clinics, or sheds for animals. The markets are Poorly equipped markets and marketing system;

iv. There is lack of market information. Farmers and other actors barely get information on trends of prices, quantity demanded, quantity supplied, and potential market shocks.

v. Lack of collective marketing culture among the rural community. Individually acting while supplying one or two animals undermines the bargaining power of farmers.

vi. Erratic taxation of livestock. In some parts of the country, farmers are charged fees, in many cases repeatedly, for each of the animals they bring to the market. Farmers are being forced to sell animals to avoid this exploitative tax on their animals.

vii. Lack of rural financing services. Farmers have limited or no sources of finacing that they depend on their livestock both as store of value and as liquid asset. This limits market orientation of livestock production in the rural areas.

viii. Limited supply for the export market. Export abattoirs are operating under limited supply of small ruminants and price distortions in the domestic markets are increasingly undermining their competitiveness.

ix. Unhealthy macro-economy with high inflation and distorted foreign exchange market. Cross-border livestock smugglers, undermining the formal export market, are exploiting the gap between the formal and parallel market exchange rates. Similarly, the high inflation is making the exporters less and less competitive in the international market.

This note also presents paradigm shifts and strategic interventions based on scientific evidence generated over the last decade.

i. Adopting a different mindset by the policy makers on the importance of marketing in the national plan of agricultural transformation. The role of the agriculture sector in the national economy cannot be enhanced without investing in agricultural marketing.

ii. Reorienting livestock production system through development and dissemination of improved livestock husbandry practices that can increase production and productivity as well as competitiveness.

iii. Creating institutional capacity in the agricultural marketing extension. The capacity of development agents working at the farmers’ level needs to be strengthened around the structure and functioning of the agricultural marketing system.

iv. Coordinating rural road construction with livestock/agricultural market development. Increased road networks connecting rural areas to urban centers and other rural areas improves access to markets, cuts on the cost of transporting animals to markets, reduces transaction costs, and information asymmetries.

v. Investing in livestock market facilities will increase the market participation and performance of livestock keepers. Thereofer, equipping livestock markets with basic facilities will have a facet of benefits both in short run and in the long run.

vi. Revising the taxation of animals brought to the market. Taxes collected per head of animal in the livestock markets should take into account the marketing behavior of the country's farmers. It should also enable them to create a culture in which they can harmonize their livestock raising according to the needs of the market.

vii. Improving access to rural financing. Rural financing services – especially those owned by the public sector – need to be integrated with livestock marketing development initiatives so that livestock keepers will be able to avoid forced selling and have better market participation.

viii. Encouraging collective action among farmers. With need based collective actions and the right support system, producers and market actors will improve their bargaining position; will be able to better network with domestic and international markets, and exploit advantages due to economies of scale.

ix. Developing broad based market information system. Well designed information systems would enable farmers and other actors trust each other more and enhance integration among markets.

x. Formulating and implementing genuine policies and legislatives to encourage the private sector. The transformation of agriculture or livestock sub-sector Ethiopia aspires to bring about cannot happen without the significant contribution of the private sector. The ongoing efforts to revise and adjust the legal framework in the country should encourage the private sector to be actively involved in livestock marketing.

xi. Livestock markets need to be under the auspices of Ministry of Agriculture. The Ministry of Agriculture, which is overseeing the development of our livestock resources, should also have a system in place to take over and manage the livestock markets from the town municipalities or offices of trade.

xii. Developing incentive mechanism for the livestock export sector. The Ministry of Agriculture and other stakeholders should put in place a careful and comprehensive incentive system to strengthen the formal livestock export trade. The incentive system needs to pay due attention to the impact of the foreign exchange market and inflation on livestock marketing.

xiii. Harmonizing policies and strategies to ensure complementarities and minimize frictions among institutions in relation to livestock marketing. All legislatives and policies formulated in the country need to take the importance of agriculture into consideration and their specific effect on the development of the sector has to be carefully analyzed.

Finally, we hope that given the dire situation the country is in, our agriculture, especially our livestock, cannot continue at its current low production and productivity levels. Therefore, we hope that the strategic interventions we have put in place and similar recommendations will be given due attention and practical actions will be taken.

# የእንስሳት ገበያ እና ግብይት ችግሮቻችንን ለመቅረፍ የቀረቡ የመፍትሄ ሃሳቦች

***በግብርና ሚኒስቴር ለግብርና ልማት ሚኒስቴር ደዔታ ጽ/ ቤት የቀረበ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ <u>፳፻፲</u> ዓ.ም.***

## የፅሁፉ ረቂቅ

*ኢትዮጵያ ሀገራችን እጅግ ግዙፍ የሆነ የእንስሳት ሀብት የታደለች ነች። ይህ ሀብት በርካታ ሚሊዮን የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ነዋሪ የኑሮ መሠረት ሲሆን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዋልታ ለሆነው የግብርናው ዘርፍም ዋና ምሰሶ ነው። ይሁንና ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ ሃብቷ እዚህ ግባ የሚባል ጥቅም እያገኘች እንዳልሆነ ይታወቃል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም አንዱና ዋናው የእንስሳት ገበያው እና የግብይት ሥርዓቱ ኋላቀር እና ያልተቀናጀ መሆኑ ነው። የግብይት ስርዓቱ አሁን ላለበት ደረጃ መንስዔ የሆኑ በርካታ ችግሮች አሉበት። ይህ ሰነድ በበግና ፍየል ግብይት ላይ ትኩረት በማድረግ ለአገር ዉስጥም ሆነ ለዉጭ ንግድ ማነቆ ናቸው ያላቸውን ችግሮች በስፋት ዘርዝሯል። ለበርካታ ዓመታት የተደረጉ ሳይንሳዊ ጥናቶችን ባጭሩ አቅርቧል። ከነዚህ መረጃዎች እና ልምዶች በመነሳትም መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ በርካታ አገር አቀፍ ስልቶችን አስቀምጧል። ሃገሪቱ ካላቸበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ግብርናችን በተለይም ደግሞ የእንስሣት ሀብታችን አሁን ባላበት ዝቅተኛ የምርት እና ምርታማነት ደረጃ ሊቀጥል አይችልም። ስለዚህ እኛ ያስቀመጥናቸው እና መሰል መፍትሄዎች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ተስፋ እናደርጋለን።*

## የእንስሳት ገበያዎች እና የግብይት ስርዓቱ ችግሮች

የኢትዮጵያ ግብርና ዋና መገለጫው ዝቅተኛ ይዞታ ባላቸው እና ግብርናቸው ሽጦ ማትረፍን ሳይሆን አምርቶ መመገብን ግብ ያደረገ በርካታ ሚሊየን ገበሬዎች[1] የሚሳተፉበት መሆኑ ነው። ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለምግብነት የሚዉሉ የቤት እንስሳት የሚረቡት ዝቅተኛ ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች ነው። ኢትዮጵያ አገራችን እጅግ ከፍተኛ እና እያደገ ያለ የእንስሳት ሃብት የታደለች እንደሆነች በሚገባ ይታወቃል[2]። ሆኖም ከዚህ ግዙፍ ሃብት ልታገኘው የሚገባትን ያህል ጥቅም እና አገልግሎት እያገኘች እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በዋነኝነት እንስሶቹ የሚረቡበት ዓላማ የገበያ ትርፍ ማግኘት ሳይሆን ለእርሻ የሚሆን የእንስሳት ጉልበት ማግኘት፣ ሃብት ማከማቻነት፣ የምግብ እና መጠጥ ምንጭነት፣ የአደጋ ጊዜ ዋስታና፣ እና የማህበራዊ ክብር መገለጫ መሆናቸው ነው።

ስለሆነም የእንስሳት እርባታ ስርዓታችን ቁጥርን እና በተወሰነ መልኩ ደግሞ ምርታማነትን ከመጨመር አኳያ ብቻ የተቃኘ ነው። እንስሳቱን የማርባቱ ተግባር የገበያውን ሁኔታ ከግምት ያላከተተ መሆኑ በአገር ዉስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ገበያ የእንስሳት ግብይታችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ አለው። የዉጭ ገበያዉን ወደታች የምናየው ሆኖ ግዙፍ ከሆነዉ እና ከእንስሳ አርቢዎች እለታዊ ኑሮ ጋር የተሳሰረዉን የአገር ዉስጥ ገበያ መጀመሪያ እናያለን። የአገር ዉስጥ የእንስሳት [በተለይ የቀንድ ከብት፣ በግና ፍየል] ገበያ ያለበት ሁኔታ እጅግ ኋላቀርና በተለይ አብዛኛው ገበሬ ከእንስሶቹ ይህ ነው የሚባል ፋይዳ የማያገኙበት ነው።

የአገር ዉስጥ ገበያ ስርዓቱ ገበሬዉን ሊጠቅም ያልቻለባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው

እናቀርባለን። ከላይ እንደ ተጠቀሰው ገበሬዎች እንስሳቱን የሚያረቡት ከገበያ ትርፍ አኳያ አቅደው ባለመሆኑ የመግዛትም ሆነ የመሸጥ ዉሳኔያቸው የግድ ትርፋማ ሊያደርጋቸው በሚችል ቀመር የተቃኘ አይደለም። የግብይት ስርዓቱን መሰረታዊ ባህርያት አለማወቅ እና የገበያዉን ዋጋ [ገበያው የሰጠዉን ዋጋ] የመቀበል ዝንባሌ በገበሬዎች ዘንድ የተለመደ ነው። ይህ የግብይት ስርዓቱን ባለበት ሁኔታ የመቀበል እና ከግብይት ስርዓቱ ዑደት ጋር የሚዛመድ የእንስሳት እርባታ ለማከናወን ተነሳሽነት አለማሳየት እንስሳት አርቢዎችን በግብይት ስርዓቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ስለዚህም እንስሳት አርቢዎችን በገበያ እና የገበያ ስራዓት ዙሪያ የተሻለ እና ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድርግ የግድ ይላል። አሁን ባለዉ እና ምርት እና ምርታማነትን ብቻ መጨመር ላይ ባተኮረ አመለካከት እና አሰራር የግብርናዉን ዘርፍም ሆነ የእንስሳት ምርታችንን ማሻሻል ወይም ለአገር እና ለህዝብ የሚጠቀም ዘርፍ ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው።

የእንስሳት ምርታችንን ከገበያ ጋር ለማቆራኘት እጅግ ወሳኝ ከሆኑት ሌሎች ጉዳዮች አንዱ የገጠር መንገድ አቅርቦት ነው። እ.ኤ.አ. አቆጣጠር በ 2019 ዓም በዓለም ባንክ የተጠና ጥናት[3] እንዳሳየው በአገራችን የተገነቡ የገጠር መንገዶች በገጠሩ ነዋሪ ወገናችን ህይወት ላይ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ለዉጥ እንዳመጡ አሳይቷል። ይህ ለዉጥ በዋነኝነት የሚመነጨው መንገድ በመሠራቱ ምክንያት ቅርበታቸው በሚጨምረው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት አማካኝነት እንደሆነ ይታወቃል። ከነዚህ ተቋምት ዉስጥ ደግሞ ዋነኛው ገበያ ነው። መንገድ ባለመኖሩ ምክንያት እንስሳት አርቢዎች መንደራቸው ዉስጥ ካለ እና ጥቂት ነጋዴዎች ከሚያዙበት ገበያ ዉጭ አማራጭ የላቸውም። የገበያው ማነስ እና በነጋዴዎች ላይ ብዙ ተቀናቃኝ አለመኖር እንስሳት አርቢዎችን ዋጋ ተማኝ ሳይሆን ዋጋ ተቀባይ ሆነው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለዉን የመንገድ ስራ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የድህነት ቅነሳዉም ሆነ የገበሬን ህይወት የመለወጡ ትግል ቁልፍ አካል ሊሆን ይገባል።

የእንስሳት ገበያዎችን እና የግብይት ስርዐቱን ለማሻሻል እና በገበያው ዉስጥ ያሉ አካላትን [በተለይ እንስሳት አርቢዎችን] በሚጠቅም መልኩ ለማጎልበት ይህ ነው የሚባል ጥረት አለመደረጉ ሌላዉ ችግር ነው። የእንስሳት ገበያዎች አብዛኛዉን ጊዜ ለሰዉም ለእንስሳም አስቸጋሪ የሆኑና ገበያተኛው ከሚገኝባቸው ቦታዎች ራቅ ብለው የተከለሉ ናቸው። በጣት ከሚቆጠሩ ገበያዎች በስተቀር እነዚህ የእንስሳት ገበያዎች አጥር እንኳን የላቸውም። ለእንስሳቱ ምንም አይነት የመኖ፣ የመጠጥ፣ የህክምና እና የጥላ አገልግሎት የላቸዉም። ለገበያተኛዉም ቢሆን የጥላ እና የመጸዳጃ አገልግሎት እንኳን የላቸዉም። ይህም ገበያዎቻችንን እንስሳትም ሆነ ገበያተኛ ብዙ ሊቆይባቸው የማይችል ስፍራዎች አድርጓቸዋል። ብዙ ሰዓት በሚያንገላታ መንገድ ተጉዘው የደረሱ ገበያተኞች እና እንስሳት በማይመች እና የበለጠ በሚያንገላታ ገበያ ብዙ መቆየት ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ሁልጊዜ ማለት ይቻላል በተቻኮለ እና በማያረካ ግብይት ምክንያት የሚገባቸውን ሳያገኙ ይቀራሉ። ባጭሩ የገበያዎች ምቹ አለመሆን የእንስሳት አርቢዎችን የገበያ ተሳትፎ እና የገበያ ላይ

---

[1] በዚህ ፅሁፍ ዉስጥ ‘ገበሬ’ የሚለው ቃል አርሶ አደሮችን አና አርብቶ አደሮችን አንዲወክል የገባ ሲሆን ከዛ ዉጭ ምንም አይነት ትርጉም አልያዘም።

[2] ምንም እንኳን የእንስሳት እና እንስሳት ምርቶች ግብይት በጣም ተወራራሽ ቢሆኑም ይሄ ሰነድ የበግ እና ፍየል ገበያ እና ግብይት ላይ ያተኩራል።

[3] Nakamura, Shohei; Bundervoet, Tom; Nuru, Mohammed. 2019. Rural Roads, Poverty, and Resilience: Evidence from Ethiopia. Policy Research Working Paper; No. 8800. World Bank, Washington, DC. © World Bank. https://openknowledge.worldbank.org/handle/10986/31495 License: CC BY 3.0 IGO.

ዉጤታማነት በእጅጉ እየተፈታተኑት ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ እንስሳት አርቢዎች የግብይት ስርዓቱን በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ በሚፈለገው ጥራት እና ወቅት አያገኙም። እንስሳት አርቢዎችም ወደ ገበያ ከመሄዳቸው በፊት ምን አይነት እና ምን ያህል እንስሳት ሻጮች ወደ ገበያ እንደሚመጡ፣ ምን አይነት እና ምን ያህል ገዢዎች ወደ ገበያ እንደሚመጡ፣ ምን ያህል እንስሳት ለገበያ እንደሚቀርቡ፣ ምን ያህል እንስሳት ሊሸጡ እንደሚችሉ፣ የዋጋ ሁኔታ እና የመሳሰሉትን በተመለከተ የተጠናቀረ እና ትክክለኛ መረጃ አያገኙም። ገበያ ላይ ምን እንደሚያጋጥማቸው መረጃ ላይ ያልተመሰረተ ግምት ይዘው የሚጓዙት እንስሳት አርቢዎች ሁልጊዜ ከነሱ የተሻለ መረጃ እና የግብይት ክህሎት ባላቸው ጥቂት ነጋዴዎችና ደላሎች ተበልጠው እና ከጠበቁት ዋጋ በታች ሸጠው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።

በአገር አቀፍ ደረጃ የገበያ መረጃ ለመሰብሰብ እየተደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም መረጃ ፋይዳ የሚኖረው ይጠቅማል ተብሎ ለሚታሰበዉ ወገን በወቅቱ እና በሚገባው መጠን ሲቀርብ ነው። አሁን እየታየ ያለው ጥረት ከዚህ አኳያ ብዙ ስራ እንደሚቀረው ግልጽ ነው። ከላይ የዘረዘርናቸውን የገበያ ባህርያት ያካተተ እና ለሰፊው ህዝብ በወቅቱ የሚደርስ የገበያ መረጃ ስርዓት ካልዘረጋን አምራቾች ከገበያዉ ስርዓት ጋር ያላቸው ትስስር (Market linkage) እና በገበያዎች መካከል ያለው መናበብ (Market integration) በጭራሽ ሊጎለብት አይችልም። ይህ ደግሞ እንስሳት አርቢዎች መቼም ቢሆን ብዙ ከሚደክሙባቸው እንስሳት እርባና ያለው ጥቅም እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል።

ሌላው የገበሬዎችን የገበያ ዉስጥ ተሳትፎ ከሚያኮስሱ ምክንያቶች አንዱ በተደራጀ እና የገበያ ጉልበት ሊፈጥር በሚችል መልክ የመንቀሳቀስ ባህል አለመኖሩ ነው። የገንዘብ እጥረት ባጋጠመው ወቅት አንድ እና ሁለት በግ ወይም ፍየል ይዞ ገበያ የሚሄድ ገበሬ ከብዙ ሻጮች መካከል የመምረጥ እድል ያለዉ ነጋዴ ፊት ከብዶ ሊታይ አይችልም። እንስሳት አርቢው ገበያ ባወጣበት ቀን መሸጥ ካልቻለ የሚደርስበትን ተጨማሪ እንግልት ጠንቅቆ የሚረዳው ነጋዴ እና ደላላ ገበሬው ከተሰጠው ዋጋ በላይ የመከራርከር አቅሙ በጣም ዉስን እንደሆነ ያዉቃል። ይህም እንስሳት አርቢዎች ከእንስሶቻቸው ሽያጭ የሚገባቸውን ያህል እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል። አሁን ባለው ሁኔታ ከቀጠለ እንስሳት አርቢዎች ሆነ የገጠር ነዋሪ ገበሬዎች በገበያ በኩል መበዝበዛቸው እንደሚቀጥል በቀላሉ መገመት ይቻላል። ስለሆነም ገበሬ እራሱ በፈቀደው እና ይመቸኛል ባለው መልኩ ተደራጅቶ እንስሳት እርባታዉንም ሆነ ግብይቱን እንዲያካሂድ መታገዝ ያለበት።

የአገር ዉስጥም ሆነ የዉጭ የእንስሳት ንግዱን እያሰናከሉት ካሉት ችግሮች ዉስጥ ሌላው የተዘበራረቀ እና ግልጽ ያልሆነ የቀረጥ ስርዓት ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ በግብርና ዘርፍ እድገት ላይ ጫና ፈጥረዋል ተብለው በተለዩ እና ከዉጭ አገር በምናስገባቸው ምርቶች እና አገልግሎቶች ሊፈቱ ይችላሉ በተባሉ ማነቆዎች ዙሪያ የቀረጥ ማሻሻያ እየተደረገ ቢሆንም በአርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ ደረጃ አሁንም ቢሆን ዉሉ የማይታወቅ ቀረጥ በእያንዳንዱ እንስሳ ላይ ከገበሬዎች ይሰበሰባል። ለምሳሌ በመንዝና ግሼ ዉስጥ አንድ በግ ወደ ገበያ በየወሩ አራት ጊዜ ቢመጣ አራቱንም ጊዜ ቀረጥ ይከፈልበታል። ይህ ተደጋጋሚ እና ምናልባትም ህጋዊ መሰረት የሌለው ቀረጥ አርሶ አደሩን እንዲበዘበዝ ከማድረጉም በተጨማሪ ተደራራቢዉን ቀረጥ መሸከም ሲያቅተው ያለፍላጎቱ እንስሳዉን ባገኘው ዋጋ ሸጦ እንዲሄድ ሊያደርገው ይችላል። ይህን የቀረጥ አሰባሰብ ስርዓት መልክ እንዲይዝ ማድረግ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖረው ወገናችን የእንስሳት ቁጥርን መጨመር የሚፈልገው የመኖ እና ህክምና ችግርን ሳይረዳ ቀርቶ አደለም። ይልቁንም የገንዘብ ተቋማት በቅርብ ስለማይገኙ እና ቢገኙም የአርሶ አደሩን አኗኗር እና ምጣኔ ሃብታዊ ባህርያት በቅጡ ያልተረዳ አሰራር ስለሚከተሉ ነው። እንስሳትን ለሃብት ማከማቻነት የሚጠቀመዉ እንስሳት አርቢ የእንስሶቹን ቁጥር የተቻለዉን ያህል መጨመር አሰፈላጊ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ይሄው ነው። ከዚህ ባሻገር የገንዘብ ተቋማት በቅርብ አለመገኘታቸው እንስሳት አርቢዉ በገበያ ውስጥ ያለዉን ነጻነት በእጅጉ ገድቦታል። ገንዘብ በፍጥነት ሊያገኝበት የሚችልበት ሌላ አማራጭ የሌለው እንስሳት አርቢ ያለው አማራጭ ገንዘብ ባስፈለገው ወቅት እንስሶቹን ይዞ ወደ ገበያ መዉጣት ነው። የማያፈናፍን የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም የገበያዉ ሁኔታ እስኪመች ለመጠበቅ እድል አይሰጥም። ስለዚህ እንስሳት አርቢው ከአጣዳፊው ችግሩ አኳያ ገበያው የሰጠዉን ዋጋ ተቀብሎ ይመለሳል። እንስሳት አርቢዉን ከዚህ የገንዘብ ተቋማት ችግር ወደ እንስሳት ቁጥር መጨመር ከዛም ወደ አስቸጋሪ ገበያ መግባት ከዛ ተመልሶ ወደ ገንዘብ ችግር እያለ ከሚሄደው አዙሪት እንዲወጣ ለማድረግ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ህዝብ አኗኗር ባገናዘበ መልኩ የተነደፈ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሲመሠረት የነበረዉን አይነት ፍልስፍና ያለው ተቋም ሊኖር ይገባል። ካልሆን አርብቶ አደሮችም ሆነ አገራችን ከዚህ ግዙፍ ከሆነው ሃብት ሊጠቀሙ አይችሉም።

ከዉጭ አገራት የምናደርገውን የእንስሳት እና የእንስሳት ምርት ግብይትም ያየን እንደሆነ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ካላት 166 ሚሊዮን[4] በላይ የስጋ እንስሳት [ከብት፣ በግና፣ ፍየል] ከ 70% በላይ ለእርድ የማይውሉ እንስት እንስሳት ሲሆን በወቅቱ ያለንን የመካከለኛ ምስራቅ የፍየል ሥጋ ገበያ የእድሜ፣ የክብደት፣ የዝርያ እና ሌሎች መስፈርቶችን ሊያሟሉ የሚችሉ የእንስሳት ቁጥር ከ3 ሚሊዮን በታች ነው[5]። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ዉስጥ ያሉ 12 ወደ ዉጭ ላኪ ቄራዎች በዓመት ከ 200 ሺህ ሜትሪክ ቶን (በወቅቱ ዋጋ 1 ቢሊየን ዶላር የሚገመት) በላይ ሥጋ አምርቶ ወደ ውጭ የመላክ አቅም ያላቸው ቢሆንም አምርተው እየላኩት ያለው ከ20 ሺህ ሜትሪክ ቶን (በወቅቱ ዋጋ 100 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት) ወይም ከ10% በታች ነው[6]። ለዚህም ዋና ምክንያቱ የውጭ ገበያው ከሚፈልገው የምርት አይነት እና ጥራት አንፃር ያለን አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ ነው ።

ለዉጭ ገበያዉ ስጋ የሚያቀርቡ ቄራዎች የሚፈልጉት የክብደት መጠናቸው ከ15-25 ኪ.ግ እንዲሁም እድሜያቸዉ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ በግና ፍየሎች ሲሆን  የአገር ዉስጥ ገበያው ደግሞ ክብደት ላይ እንጂ እድሜ ላይ ብዙም ትኩረት የማያደርግ ሸማች የሚበዛበት ነው። በአሁን ወቅት 1 ኪ.ግ ሥጋ ወደ ውጭ የሚሸጥበት ዋጋ 5.45 የአሜሪካን ዶላር (በወቅቱ ምንዛሬ 253 ብር) በኪሎግራም ሲሆን ወደ ዉጭ የስጋ ምርት የሚልኩ ቄራዎች እንስሳትን ከገበያ የሚገዙት 260 ብር በኪሎግራም ነው። የሥጋ ምርትን ከውጭ ለማስገባት ከፍተኛ ቀረጥ በመኖሩ እንጂ ሀገራችን ሥጋን በከፍተኛ ሁኔታ ከውጭ ከሚያስገቡ ሀገራት አንዷ ልትሆን እንደምትችል አመላካች ሁኔታዎች ይታያሉ። ለምሳሌ ከቀረጥ ነፃ ምርቶችን የማስገባት ፈቃድ ያለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ 1 ኪ.ግ ሥጋ ከውጭ ከ4 የአሜሪካን ዶላር (በወቅቱ

[4] Federal Democratic Republic of Ethiopia. Central Statistical Agency Agricultural Sample Survey 2020/21 [2013 E.C.]. Volume II. Report on Livestock and Livestock Characteristics. (Private Peasant Holdings). Statistical Bulletin, 589. Addis Ababa, Ethiopia.

[5] Federal Democratic Republic Of Ethiopia Central Statistical Agency Central Statistical Agency Agricultural Sample Survey Agricultural Sample Survey 2018/19 [2011 E.C.]

[6] Ethiopian Meat and dairy industry development institute , Annual report 2019

ምንዛሬ 186 ብር) በታች በሆነ ዋጋ ሲያስገባ ቆይቷል[7]።

በሌላ መልኩ ህጋዊ የሆነው የዉጭ ንግድ ላይ ትልቅ ማነቆ የሆነው ህገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድ (informal livestock trade) ሲሆን የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የጎረቤት ሀገራት ወደ ውጭ ከሚልኩት እንስሳት (በዓመት ከ2- 4 ሚሊዮን ) ውስጥ ከ 60% ከመቶ በላይ ከሀገራችን በህገወጥ መንገድ የወጣ ነው[8]። የሀገራችን ቆላማ አካባቢዎች ከበርካታ የጎረቤት ሀገራት ጋር ስለሚዋሰኑና በጎረቤት ሀገራት ካለው የገበያ ሳቢነት የተነሳ በህገወጥ መንገድ በቁም ወደ ውጪ ሀገራት ገበያ የሚቀረቡ እንስሳት እጅግ በርካታ ናቸው። የገቢዎች ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ ባለፉት አራት አመታት በየአመቱ በአማካኝ 304000 በጎችና ፍየሎችን በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ ገበያ አቅርባለች፡፡ ሆኖም የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በህገወጥ መንገድ ወደ ውጪ ገበያ የሚቀርቡ እንስሳት ቁጥር በህጋዊ መንገድ ለውጪ ገበያ በቁም ከሚቀርቡት እንስሳት በሰባት እጥፍ ይበልጣሉ። ይኸውም በአማካኝ 2.1 ሚሊዮን በጎችን ፍየሎች በህገወጥ መንገድ ከሀገራችን ወደ ውጪ ገበያዎች የመነሻ ስማቸውን በመቀየር (ከሌሎች ሀገራት እንደተነሱ በመመዝገብ) ይላካሉ[9]። ይህን ህገወጥ ንግድ ለመከላከል ለረጅም ጊዚያት በመንግስት ከፍተኛ ቁጥጥር ቢደረግም ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት አልተቻለም። የህገወጥ ንግዱ ዋናው ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ሲሆን በባንክ እና በትይዩ ገበያው ያለው የውጭ ምንዛሬ ልዩነትም ቁልፍ መንስዔው ነው። እንስሳቱ በህገወጥ መንገድ ከሀገር ወጥተው ሲሸጡ ሽያጩ በትይዩ ገበያ ባለው የውጭ ምንዛሬ ዋጋ ስለሚሆን በህጋዊ መንገድ ከሚያገኙት ከ35% በላይ ክፍያ ያገኛሉ ማለት ነው[10]።

የመዳረሻ ገበያ ውስንነትም ከእንስሳት ሀብታችን ተገቢውን ጥቅም እንዳናገኝ ካደረጉን መሰረታዊ ችግሮች አንዱ ነው። በወቅቱ ያለን መዳረሻ ገበያ መካከለኛው ምስራቅ (95% ሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ) ሲሆን የነዚህ ገበያዎች ፍላጎት ከ90% በላይ የፍየል ሥጋ ነው[11]። በዚህም ምክንያት በሁለቱ ሀገራት በሚፈጠሩ የገበያ ችግሮች አጠቃላይ የሀገራችንን የእንስሳት ግብይት በከፍተኛ ሁኔታ ሲጎዳ በተጨባጭ ታይቷል። በመሆኑም አዲስ የመዳረሻ ገበያ መፍጠር የንዑስ ዘርፉ ቁልፍ ተግባር ሊሆን የሚገባ ሲሆን ለዚህም የጤናና ጥራት መስፈርቶችን ማሟላት እና በዋጋ ተወዳዳሪ መሆን ይገባል።

ይሁን እንጂ በወቅቱ ያለውን ሁኔታ ስናይ የጤናና ጥራት መስፈርቶችን በማሟላት እና በዋጋ ተወዳዳሪ በመሆን አዲስ መዳረሻ ገበያ መፍጠር ይቅርና አሁን ያሉንን መዳረሻ ገበያዎች በተወዳዳሪ ሀገራት (ለምሳሌ ኬንያ) እየተነጠቅን እንገኛለን። ይህም እየሆነ ያለው በዋናነት የእንስሳት እርባታ ስርዓታችን ከገበያ ጋር ያለዉ ዝቅተኛ ትስስር፣ መላ ያልተበጀለት የዋጋ ንረት ጉዳይ፣ እና በሀገራችን ያለው የመደበኛ እና ኢመደበኛ የዉጭ ምንዛሬ መጠኖች ልዩነታቸው የተጋነነ መሆኑ ነው። የዋጋ ንረቱ በፍጥነት መላ ካልተበጀለት በዉጭ ገበያ ዉስጥ ያለንን ትንሽም ድርሻ በፍጥነት ሊያሳጣን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። በዉጭ ምንዛሬ ተመን ረገድ የሚታየው ጤናማ ያልሆነ የገበያ ባህርይ የህገ ወጥ የእንስሳት ንግዱን በሞተርነት እያንቀሳቀሰው እንደሆነ ተገንዝበን ባስቸኳይ ምጣኔ ሃብታዊ እርምጃ መዉሰድ ያስፈልገናል። በዚህ ሰነድ ዉስጥ የዋጋ ንረት እና የውጭ ምንዛሬ ጉዳዮችን ለጊዜው ትተናቸው በግብርና ሚኒስቴር ህጋዊ ስልጣን ዉስጥ ሊሰሩ የሚችሉት ላይ ብቻ እናተኩራለን።

## በእንስሳት ገበያ እና ግብይት ስርዓት ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ያላቸው ፋይዳ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ዉጤት

የእንስሳት ግብይት ስርዓቱን ማሳደግ ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ እንዳለዉ በርካታ ጥናቶች አሳይተዋል። አስፈላጊ ከሆነ ዝርዝሩን በሌላ መልኩ የምናቀርብ ሆኖ የሚከተሉትን ቁልፍ ሳይንሳዊ ሃቆች እናቀርባለን፡

- አሁን ባለዉ የግብይት ስርዓት ዉስጥ የሚሳተፉ እንስሳት አርቢዎችም ሆነ ሌሎች ገበያተኞች ማግኘት የሚገባቸውን ገቢ እና ትርፍ እያገኙ አይደለም። እ.ኤ.አ. አቆጣጠር በ2019 ዓም በ International Center for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA) የተደረገ ጥናት እንዳሳየው በተመረጡ የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ገበሬዎችና እና አዲስ አበባ ላይ ያሉ የበግ/የፍየል ነጋዴዎች የሚሸጡበትን ዋጋ የኛ በጎች/ፍየሎች ወደ ጅቡቲ በሚገቡበት ወቅት ድንበር ላይ ካላቸው ዋጋ ጋር በማነጻጸር በእሴት ሰንሰለቱ [value chain] ዉስጥ ያለዉን የዋጋ መበረዝ (price distortion) አሳይቷል። በጥናቱ መሰረት ገበሬዎቻችን አሁን ባለው የግብይት ስርዓት ብልሹነት ምክንያት ከበግ እና ፍየል ሽያጭ በቅደም ተከተል ሊያገኙ ይገባቸው ከነበረው በ68% እና 57% ያነሰ ዋጋ ይከፈላቸዋል። የአዲስ አበባ ነጋዴዎችም ቢሆን ድንበር ላይ ካለዉ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከበግ እና ፍየል ሽያጭ በቅደም ተከተል በአማካይ 33% እና 17% ያነሰ ክፍያ ይከፈላቸዋል። የዚህ ልዩነት ዋና መንስዔ በደንብ ያልተጠኑ የመንግስት ደንብ እና ፖሊሲዎች ናቸው። ለምሳሌ እንስሳት አርቢዎች በአገሪቱ ዉስጥ ያዋጣናል በሚሉት ቦታ እና ጊዜ ያለምንም ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጫና መሸጥ አለመቻላቸው የዚህ ክፍተት አንዱ መገለጫ ነው። ሌላው የበግ እና ፍየል ነጋዴዎችን ባላቸው አቅም እና ፍላጎት መጠን በገበያ ዉስጥ እንዲንቀሳቀሱ እና ከሚገዙባቸው ትንንሽ ገበያዎች ጀምሮ የሚያበረታታ ድጋፍ ቢደረግላቸው ይህን ክፍተት ማጥበብ ይቻላል። ይህ ትልቅ ክፍተት እንሳስት አርቢዎችን እና ህጋዊ ነጋዴዎችን ከመጉዳቱ ዉጭ በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ተሻጋሪ የእንስሳት ንግድ ዉስጥ የሚሳተፉ ሰዎችንም የሚያበረታታ ነው።
- የእንስሳት ገበያዎች ዉስጥ ወይም ገበያዎቹ በሚገኙበት አካባቢ ሊሰጡ የሚገቡ አገልግሎቶች በገበሬዎችም ሆነ በሌሎች ገበያተኞች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው። እ.ኤ.አ. በ2020 እና 2021 የታተሙ የ ICARDA የምርምር ሥራዎች እንዳሳዩት በአገር አቀፍ ደረጃ የእንስሳት ህክምና መስጫ፣ የታጠሩ የገበያ ጥላዎች፣ እና የዉሃ መጠጫ ገንዳዎች የበግ እና ፍየል ግብይት ዉስጥ የሚሳተፉ አካላት እጅግ የሚፈልጓቸው አገልግሎቶች ናቸው። [12] በመንዝና ግሼ አካባቢ ያሉ የበግ እና ፍየል ገበያተኞች ላይ በተለይ የተደርገ ጥናት ደግሞ ጊዜያዊ ማቆያ በረት ከሁሉም የበለጠ ተፈላጊ አገልግሎት እንደሆነ አሳይቷል። በጥናቱ መሰረት ገበያተኞቹ ለጊዜያዊ ማቆያ በረት ለመክፈል የወሰኑት መጠን ለዉሃ ገንዳዎች፣ ለመኖ አቅርቦት አገልግሎት፣ ለእንስሳት ጤና አገልግሎት፣ ለገበያተኛ መጸዳጃ ቤት፣ ለታጠሩ የገበያ ጥላዎች፣ እና ላልታጠሩ የገበያ ጥላዎች ሊከፍሉ ከፈቀዱት ጋር ሲነጻጸር በቅደም ተከተል 1.77, 1.74,

---

7 Ministry of trade and industry . market opportunity and linkage with Ethiopian airlines ,2017

8 Common Market for Eastern and Southern Africa .Comprehensive African Agriculture Development Programme POLICY BRIEF Number 2 February 2009.

9 Tesfaye, A., & Amaha, N. (2018). A Review on Cross-Border Livestock Trade Across Dry Land Borders of Ethiopia: The Trends and Implications.

10 Personal communications with livestock exporters in Addis Ababa. 2021.

11 Ethiopian Meat and dairy industry development institute, challenges and posibile solutions of Ethiopian meat sector, 2017

12 Kassie G T, Zeleke F, Birhanu M, and Scarpa R. 2020. Reminder Nudge, Attribute Nonattendance, and Willingness to Pay in a Discrete Choice Experiment. Agricultural and Applied Economics Association (AAEA) Conferences, 2020 Annual Meeting, July 26-28, Kansas City, Missouri. DOI: 10.22004/ag.econ.304208.

1.23, 1.09, 2.0 እና 2.27 እጥፍ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።[13] ይሄ የጊዜያዊ በረት ማቆያ ዋና ጥቅሙ ከብቶችን ለመንዳት እንዲቀል አጅበው የሚመጡ እንስሳትን ወደ ገበያ ዉስጥ እንዳይገቡና ከላይ የተጠቀሰው ተደጋጋሚ ቀረጥ ሰለባ እንዳይሆኑ ማስቻል ነው። ለጊዜያዊ በረቶቹ ያለው ፍላጎት እንስሳት አርቢዎች በቀረጡ ምን ያህል እንደተማረሩ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

- ከነዚህ የገበያ ውስጥ አገልግሎቶች አንዱ የሆነዉን የገብያ ጥላ በዘጠኝ የበግ እና ፍየል ገበያዎች ላይ በመገንባት እና ለሁለት ዓመት የተመረጡ በግ እና ፍየል አርቢዎችን በመከታተል የተደረገ ጥናት እንዳሳየው የገበያ ጥላ ብቻ በመገንባቱ በገበያዉ የሚጠቀሙ አርቢዎች የገበያ ተሳትፏቸው [ወደገበያ በሚወስዱት በግና ፍየል ቁጥር ሲለካ] በ14% ያደገ ሲሆን ከበግ እና ፍየል የሚያገኙት ገቢ በ40% ጨምሯል።

- እ.ኤ.አ. አቆጣጠር በ2018 ዓ.ም. በICARDA የተሠራ ጥናት ለአንድ ዓመት ያህል ለበግ እና ፍየል አርቢዎች በሸማቾች ተመራጭ የሆኑ የበግ እና የፍየል ባህርያትን (traits)፣ በገበያው ለተለያዩ የበግ እና የፍየል አይነቶች ይኖራል ተብሎ የሚገመተዉን ዋጋ፣ ለገበያ የቀረበዉን በግና ፍየል ቁጥር፣ የተሸጠዉን የበግ እና ፍየል ቁጥር፣ የገበያ አገልግሎቶች መኖር እና አለመኖር፣ እና ድንገተኛ የሆኑ ማህበራዊ ወይም የተፈጥሮ ክስተቶችን በተመለከተ መረጃ በመላክ የግብይት ባህርያቸው ላይ የሚኖረዉን ለዉጥ ገምግሟል። ይህ ጥናት የሚከተሉት የግብይት ባህርያት ላይ ለዉጥ እንዳለ አሳይቷል፤
  - እንስሳት አርቢዎች ያገኙትን መረጃ ከሌሎች አርቢዎች ጋር በመጋራት ገበያን በተመለከተ ፋይዳ ያለው ዉይይት አድርገዋል።
  - በግብይት ስርዓቱ ዉስጥ ያላቸው ጉልበት እንደ ጨመረ እና ገበያ ዉስጥ ጥሩ ስሜት እንደሚሰማቸው ገለጸዋል።
  - ስለገበያው የተሻለ ግንዛቤ ስላላቸው የመሸጥም ሆነ የመግዛት ዉሳኔያቸውን በጥንቃቄ እና ያለ ጥድፊያ ማከናወን ችለዋል።
  - እንስሳት አርቢዎች ወደ ገበያ ሲሄዱ ያለ ስጋት እና ምን ያጋጥመኝ ይሆን ከሚል ስሜት ዉጭ ሆነው እንደሆነ ገልፀዋል።
  - በነጋዴዎች እና በደላሎች ይደርስባቸው የነበረው ወከባ አሁን ብዙም እንደማይረብሻቸው ገልጸዋል።
  - እንስሳት አርቢዎች ተመሳሳይ መረጃ ስለ ትልልቅ የበግ እና ፍየል ገበያዎች ማግኘት እንደሚፈልጉ አሳውቀዋል።

  ይህ የሚያሳየው እንኳን ሰፋ ያለ ይዘት ያለው እና ወቅታዊ መረጃ ቢቀርብላቸው እንሳስት አርቢ ወገኖቻችን ባጭር ጊዜ ዉስጥም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ የባህርይ ለዉጥ ሊያመጡ እንደሚችሉ ነው።

- የተሻሻሉ በግ እና ፍየሎችን ለገበያ በማቅረብ ዙሪያ የተሰባሰቡ አርሶ አደሮች በግላቸው ከሚንቀሳቀሱት አንጻር ሲታይ ከእንስሣት ሃብታቸው የሚያገኙት ገቢ ጉልህ የሆነ ለዉጥ አለው። ICARDA ለአስር አመታት ያህል በአበርገሌ፣ በመንዝ፣ ዶዮገና እና በንጋ አያካሄደ ያለው የተቀናጀ የበግ እና ፍየል ምርምር በተለይ ደግሞ የማህብረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ ስራ እና ከ International Livestock Research Institute [ILRI] ጋር በትብብር የሚያደርገው የአንድ መንጋ የእንስሳት ጤና [one herd health] ተግባራዊ ምርምር ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ተረጋግጧል። እ.ኤ.አ. አቆጣጠር በ 2021 ዓ.ም. የታተመ የምርምር ጽሁፍ እንደሚያሳየው የማህብረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ ስራ ላይ የሚሳተፉ በግና ፍየል አርቢዎች ከማይሳተፉት ጋር ሲነጻጸር በአማካይ 18 በግ/ፍየል ተጨማሪ ለገበያ ያቀረቡ ሲሆን በነፍስ ወከፍ ያገኙት አመታዊ ገቢም 20.6% ያህል የበለጠ እንደሆነ ታይቷል። በተመሳሳይ የተሻሻለዉን የእንስሳት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ተጠቃሚ የሆኑ በግ እና ፍየል አርቢዎች ከማይጠቀሙት ጋር ሲነጻጸር በአማካይ 18 በግ/ፍየል ተጨማሪ ለገበያ ያቀረቡ ሲሆን በነፍስ ወከፍ ያገኙት አመታዊ ገቢም 21% ያህል የበለጠ እንደሆነ ታይቷል።

እነዚህ የምርምር ስራዎች የዚህ ሰነድ አቅራቢዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተሳተፍንባቸዉና ለምንሰነዝራቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ጥሩ መነሻ ይሆናሉ ያልናቸው ብቻ ናቸው። ስለዚህ የእንስሳት ገበያን እና ግብይትን ማሻሻል ምን ያህል ፋይዳ እንዳለው ለማሳየት የተሰሩ እና እየተሰሩ ያሉ ምርምሮች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ለማስታወስ እንወዳለን።

## ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የመፍትሄ ሃሳቦች

ከላይ በተጠቀሱት ሳይንሳዊ መረጃዎች መነሻዎች አርሶ አደሮችን በግብይት ስርዓቱ ዉስጥ የበለጠ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ኢንዲሆኑ ለማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች እናቀርባለን፤

1. በቅድሚያ ገበያ ልማት እና የገበያ ስርዓት ግንባታ በእንሥሣት ብሎም በግብርና ዘርፍ ልናመጣ ለምናስበዉ እመርታ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት እና በጭራሽ ችላ ልንለው የማንችለው ጉዳይ እንደሆነ ከግንዛቤ መግባት አለበት። አንድም የምርት እና የአገልግሎት ዘርፍ ገበያውን እና የግብይት ስርዓቱን ሳያዘምን ዘመናዊ የሆነ ወይም እና አገልግሎቱ ተጠቃሚ በሆኑ አካላት ዘንድ ያለዉን ተቀባይነት ይዞ የቆየ የለም።

2. የዘርፉ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የእንስሳት እርባታ ስርዓታችንን ማሻሻል እና ገበያ ተኮር ማድረግ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣል። በመሆኑም ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የእርባታ ማሻሻያ ስራዎችን ማከናወን የግድ ይላል። ከዚህም ውስጥ አንዱ በተለያዩ የሀገሪቷ ክልሎች በልማት አጋሮች (ለአብነት ICARDA) ድጋፍ የተጀመሩ ማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻል ፕሮግራም አንዱ ነው። በዚህ ፕሮግራም እየተገኙ ያሉ ውጤቶች በተለይም በአጭር ጊዜ ውስጥ የዉጭ ገበያው የሚፈልገውን የክብደት መጠን የሚያሟሉ ዝርያዎችን (በ 3 ወር ውስጥ 15 -25 ኪሎግራም ማድረስ) በገበሬዎች ደረጃ ማርባት መቻሉ ጥራት ያለው በግና ፍየል በተመጣጣኝ ዋጋ ለዉጭ ገበያ አቅራቢ ቄራዎች ማቅረብ እንደሚቻል አመላካች ነው። በመሆኑም እነዚህን በየአካባቢው ያሉ ጅምር ሥራዎች በልዩ ትኩረት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች እንዲስፋፉ እና እንዲተገበሩ ቢደረግ በዘርፉ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ ይቻላል።

3. የግብርና ስርጸት ስርዓቱ የግብይትን አጀንዳ ተገቢዉን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በየቀበሌው የሚገኙ የልማት ጣቢያ ሰራተኞችም የግብይት ስርዓት ምንነት እና ልማትን በተመለከተ ያላቸው አቅም ሊገነባላቸው ይገባል። እነዚህ የገበያ ባለሙያዎችም ገበሬው የተሻለ እንስሳት አርቢ እንዲሆን ከሚደረገዉ እገዛ ጎን ለጎን ያሉትን እንስሳት በተገቢው ቦታ እና ጊዜ እንዲሸጥ የማስቻል ሥራ ሊሰሩ ይገባል።

4. የገጠር መንገድ ልማት ስራ ከግብይት ስርዓት እድገት ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲተገበር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚሰራበት ሂደት መፈጠር አለበት። የሌሎች አገሮች የመንገድ ልማት ልምድ ቢጠና እና ገበያን ከማሳደግ አኳያ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጥ ከግንዛቤ ቢገባ።

[13] Zeleke F, Kassie G T, Haji J., and Legesse B. 2020. Preference and Willingness to Pay for Small Ruminant Market Facilities in the Central Highlands of Ethiopia, Journal of International Food & Agribusiness Marketing, DOI: 10.1080/08974438.2020.1838385.

5. የገበያ ልማት ለግብይት ስርዓት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ከግምት ገብቶ የእንስሣት ገበያዎች አስፈላጊው ትኩረት ቢሰጣቸዉና የእንስሣት ህክምና፣ የመኖ ማቅረቢያ፣ የዉሃ መጠጫ፣ የገበያ ጥላ፣ የማቆያ በረት፣ እና የሽንት ቤት አገልግሎቶች በገበያዎች አካባቢ የሚገነቡበት አሰረራ ቢዘረጋ።

6. በእንስሳት ግብይት ሂደት ዉስት የሚሰበሰብ ቀረጥ የአገሪቱን አርሶ አደሮች የግብይት ባህርይ እና እንቅስቃሴ ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል። በተጨማሪም ወጥ በሆነ መልኩ ከገበያዉ ፍላጎት አንጻር የእንስሣት ምርታቸውን የሚቃኙበት ባህል መፍጠር እንዲችሉ የሚያደርግ መሆን አለበት። ከላይ ባጭሩ የተቀመጡ የጥናት ዉጤቶች እንዳሳዩት በአገሪቱ ዉስጥ የሚገኙ የእንስሳት ሃብት ምርት እና ግብይት ዉስጥ የሚሳተፉ አካላት ብዙም መጠቀም ያልቻሉበት አንዱ ምክንያት ይሄ ወጥነት የጎደለዉ እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ የቀረጥ አሰባሰብ ነው። የድንበር ገበያ ባለባቸው አካባቢዎች እየታየ ያለው ከፍተኛ የሆነ የኮንትሮባንድ ንግድም ቢሆን ዋናዉ መንስዔ ይሄው ነጋዴዎችን እና ገበሬዎችን የማያበረታታ አሰራር ነው።

7. የእንሳሳት ግብይት እንደማንኛዉ ትልቅ የማምረት እና የንግድ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴ ዉጤታማ ለመሆን እና በፍጥነት ለመራመድ ከብድር ገበያው ጋር ተቀናጅቶ መሥራት የሚችልበት ስርዓት መዘርጋት አለበት። ገበሬዎችም ሆኑ ነጋዴዎች ከገበያዉ ፍላጎት እና ወቅታዊ ባህርያት አንጻር መንቀሳቀስ እንዲችሉ የገንዘብ አቅማቸውን ብሎም የገበያ ተሳትፏቸውን የሚያጎለብት የብድር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል።

8. የግብርናው ዘርፍ ካለው አቅም እና ለዚህች ሀገር ሁለንተናዊ እጣ ፈንታ ወሳኝ መሆኑ በአገሪቱ መሪዎች ዘንድ በሚገባ ግልጽ መሆን አለበት። ከዚህም ባሻገር በአገሪቱ የሚወጡ ህጎችና ደንቦች ሁሉ በግብርናው ዘርፍ [በተለይ በእንስሣት] ምርት እና ግብይት ላይ የሚኖራቸዉን ተጽእኖ በጥቃቄ የሚገመግምና ለዉሳኔ የሚያቀርብ አካል ተመስርቶ መንቀሳቀስ አለበት። ከገበሬው ማሳ እስከ አለም አቀፉ ገበያ ድረስ ያለዉን የግብይት ስርዓት የገመገሙ ጥናቶች አንዳሳዩት አሁን ያለዉ አሰራር አርሶ አደሮች እና በአዲስ አበባ የሚገኙ የበግ እና የፍየል ነጋዴዎች ሊያገኙ ከሚገባቸው እጅግ ያነሰ ክፍያ እንድሚያገኙ ታዉቋል። ይሄም ተደምሮ አገራችን ከእስሣት ሃብቷ ማግኘት የሚገባትን አለማግኘቷን ያስረዳል።

9. አርሶ አደሮች በግብይት ሂደቱ ዉስጥ ያላቸው ተሳትፎ ኢንዲጎለብት እና ከምርታቸው የሚያገኙት ገቢ ኢንዲጨምር ምርታቸውን እና የግብይት ተግባራቸውን በቅንጅት እና በህብረት እንዲያከናዉኑ ማገዝ ያስፈልጋል። በአገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንዳየነው የአርሶ አደሮች ማህበራት የፖለቲካ አስተሳሰብ ዉጤት እና መገልገያ ሆነው ቆይተዋል። ይሄም በገበሬዎች እና በሌሎች አካላት መካከል የህበረት ስራን በተመለከት ከፍተኛ ጥርጣሬ እና ብዥታ እንዲፈጠር አድርጓል። ስለዚህ ገበሬዎች በራሳቸው ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሰረተ እና በግብይት ስርአቱ ዉስጥ ጉልበት እንዲኖራቸው በሚያስችል መልኩ በጋር የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል። የምርት እና ግብይት ማህበራትን ገበሬዎች በሚፈልጉት መጠን እና ይዘት ማቋቋም ኢንዲችሉ ማገዝ እና ከማንም በኩል ምንም አይነት ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር መከላከል ያስፈጋል።

10. የገበያ መረጃ ስርዓት  በጥንቃቄ ተነድፎ እና ታስቦበት ሊመሰረት ይገባል። ይህ የመረጃ ስርዓት ገበሬዎችን የምርት እና ግብይት ባህርያት፣ በአገሪቱ ዉስጥ ያሉ የእንስሣት ገበያዎችን ይዘት፣ በገበያዉ ሰንሰለት ዉስጥ ያሉ ዋና ዋና አካላትን ጥንካሬና ፍላጎት፣ የግብይት ስርዓቱ ከቦታ እና ከጊዜ አኳያ ያሉትን ባህርያት፣ እና የግብይት ስርዓቱን ቁልፍ ገጽታዎች [የአቅርቦት መጠን፣ የፍላጎት መጠን፣ የዋጋ መጠን አና ባህርይ፣ ለግብይት የቀረቡ ምርቶች ገጽታ፣ የገዢ እና ሻጭ ብዛት እና አይነት፣ ወዘተ] ከግምት ያስገባ መሆን አለበት። ከቅርጹ እና እንቅስቃሴው እኩል ለእንስሳት አርቢዎች እና ለሌሎች በግብይት ስርአቱ ዉስጥ ለሚሳተፉ አካላት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ከጅምሩ ሊታሰብበት ይገባል።

11. በማንኛዉም የምጣኔ ሃብት ስርዓት ዉስጥ መሠራት ያለበትን መሰረተ ልማት በተገቢው ሰአት እና ቦታ አለመስራትን ያህል አገርን እና ህዝብን ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ጉዳይ ምናልባት ከጦርነት ዉጭ ላይገኝ ይችላል። ስለዚህ የእንስሣት ግብይት ስርዓትን ለማጎልበት የሚያስፈልጉ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊሰሩ የሚገባቸው ተቋማትና መሰረተ ልማቶች አለመስራታቸው ለእንስሣት ምርትም ሆነ ለግብርናው ዘርፍ ዕድገት እንቅፋት እንደሆነ ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል። ስለሆነም የእንሥሳት ዘርፍ ልማት ላይ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች እና ደንቦች ከምርት እና ምርታማነት ማሳደግ እኩል የግብይት ስርአቱን ማሳደግ ላይም ተገቢዉን ትኩረት በሰጠ መልኩ ቢነደፉ ወይም ቢከለሱ ከብዙ ድካም እና ልፋት ያድኑናል።

12. እንደ ማንኛዉም የምጣኔ ሃብት ደረጃው ያደገ ማህበረሰብ የግብርናችንም ሆነ የእንስሣት ምርት ዘርፎች ለውጥ እና ብልጽግና ከግሉ ዘርፍ ጉልህ አስተዋጾ ዉጭ በጭራሽ ሊሳካ አይችልም። በተለይ የግብይት ስርአቱን አድገት መሪ መሆነ የሚችለው የግሉ ዘርፍ ነው። ስለዚህ አሁን በአገራችን እየተደረገ ያለው የህግ መሰረቶችን የመከለስ እና የማስተካከል ጥረት የግሉን ዘርፍ በእንስሳት ግብይት ዉስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያበረታቱ መሆን አለባቸው። በአገራችን ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየው እና የመንግስትን ተቋማት የምጣኔ ሃብት ሁለንተናዊ ባለቤት እና አንቀሳቃሽ አድርጎ የማሰቡ ሂደት በዘመናዊ እና ትርጉም ባለዉ አሳታፊ ስርዓት  መተካት ይዋል ይደር ልንለው የማንችለው ጉዳይ ነው። የግሉ ዘርፍ ትርፍ ከማግኘት አንጻር የሚንቀሳቀስ ስለሆነ የምርት ኃይሎችን በአግባቡ እና በጥንቃቄ እንደሚጠቀም በጣም ግልጽ ነው። ከግብይት ስርዓት የመጨረሻ ግብ አኳያ የግሉ ዘርፍ እንጂ የመንግስት ተቋማት በተሳታፊነት ዘለቄታዊ ፋይዳ እንደማይኖራቸው ግልጽ መሆን ይኖርበታል። ለእንሳስት ግብይት ዕድገት ገበሬዉን ማዕከል ያደረገ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታዎችን በአፋጣኝ ማስፋፋት ይገባል። ይህንንም  በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ልማት ስልት በመንደፍ እና አመቺ ሁኔታ በመፍጠር የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ዘርፉ የመሳብ ጥረት በደንብ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ከዓመታት በፊት በ ሆርቲካልቸር (አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ አበባ፣ ወዘተ) ልማት ላይ የተሰራውን የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ሞዴል አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

13. የእንስሳት ገበያዎች ብዙውን ጊዜ የሚመሰረቱት ለሰዉም ለእንስሳትም አስቸጋሪ በሆኑ ቦታዎች ላይ ነው። መሬትም በመንግስት ባለቤትነት ከመያዙ አንጻር በሃላፊነት እና በባለቤትነት ስሜት ተነሳስቶ ገበያዎችን ለማልማት የሚደረግ ጥረት በመላ አገሪቱ በጭራሽ አይታይም። የመሬት ይዞታ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ በአገሪቱ የሚገኙ የእንስሳት ገበያዎች የሚለሙበት እና በአስፈላጊ [ከላይ የተጠቀሱ] አገልግሎቶች እንዲታገዙ የሚያስችል አስራር መዘርጋት አለበት። የገበያ ቦታዎችንም የእንስሳት ሃብታችን ልማት በበላይነት እየመራ ያለው የግብርና ሚኒስቴር ከማዘጋጃ ቤቶች ተረክቦ የሚያስተዳድርበት አሰራር መፈጠር አለበት። አለበለዚያ የእንስሳት ገበያዎች በማንኛዉም የከተማ ልማት እቅድ ዉስጥ ትኩረት ተነፍጓቸው እንደሚቀሩ የእስካሁኑ ሂደት በቂ ማስረጃ ነው።

14. የእንስሳት እርባታ ሂደት እንዳይስተጓጉል ከማሰብ አንፃር እንስት እንስሳት ለእርድ አገልግሎት እንዳይውሉ የሚከለክል ህግ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በመሰረቱ ህጉ የዘርፉን የእርባታ ሂደት ከማስጠበቅ አንፃር የወጣ በመሆኑ በአዎንታዊ ጎኑ መመልከት ይገባል። ይሁን እንጂ ሀገሪቷ ካላት የእንስሳት ሀብት 70% በላይ እንስት በሆነበት እና በተለያዩ ምክንያቶች ምርታማ ያልሆኑ

እንስት እንስሳት[14] በሚኖሩበት ሁኔታ በጅምላ ተግባራዊ ማድረጉ በእንስሳት አቅርቦቱ ላይ የራሱ የሆነ ችግር ፈጥሯል። በእድሜና በተለያዩ ምክንያቶች መውለድ ያቆሙ እና የምርት ችግር ያለባቸውን እንስት እንስሳት ይዞ መቆየት ውስን የሆነውን የመኖና ሌሎች የእርባታ ግብዓቶችን ከመሻማት ውጭ ለዘርፉ ትርጉም ያለው አስተዋፆ የለውም። በመሆኑም ለእርባታ የማይውሉ እንስት እንስሳትን ለእርድ አገልግሎት መዋል የሚችሉበትን ስርዓት በመዘርጋት የእንስሳት አቅርቦትን ማሳደግ ይቻላል።

15. የግብርና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ህጋዊ የሆነው የዉጭ ንግድ ተገቢዉን ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል። እንስሳት እና የእንስሳት ምርት ወደ ዉጭ የሚልኩ አካላት አሁን ባለዉ ሁኔታ በኪሳራ ከመዘጋት የሚታደጋቸው የለም። ወይም ደግሞ ንግዱ ላይ ለመቆየት እነሱም ህገ ወጥ ወደሆነ ተግባር ሊገቡ ይችላሉ። ስለዚህ ሰፊ መሰረት ያለው የገበያ እና ግብይት ስርዓት ማሻሻያ መነደፍ እና ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል። ይህም ማሻሻያ ህገ ወጥ ነጋዴዎችን ወደ ህጋዊዉ መንገድ እንዲመጡ የሚያስችል እና ህጋዊ ነጋዴዎችም በህጋዊዉ መንገድ እንዲቀጥሉ የሚያበረታታ መሆን ይኖርበታል። በተለይ የዉጭ ምንዛሬ ገበያዉ እና የዋጋ ንረቱ በዘርፉ ላይ የሚኖረዉን ተጽዕኖ በጥንቃቄ በመገምገም ስልቶችን መንደፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የውጭ ምንዛሬ ልዩነቱን መሰረት ያደረገ የዉጭ ንግድ ማበረታቻ (ድጎማ) በማድረግ ህጋዊዉን ንግድ ማገዝ ይቻላል። ይህን በማድረግ ችግሩን መፍታት ከተቻለ ከሁለት ሚሊዮን በላይ እንስሳትን ወደ ሀገር ውስጥ ግብይት በመመለስ ለኢንዱስትሪው የሚቀርበውን ግብዓት በእጥፍ በማሳደግ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በእጥፍ (80 ሚሊዮን ዶላር) ማሳደግ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል። ይህ የአሰራር ስርዓት በሌሎች ሀገወጥ ንግድ በከፍተኛ ሁኔታ በሚስተዋልባቸው የኤክስፖርት ምርቶች ላይ ተግባራዊ ተደርጎ ተጨባጭ ለውጥ መምጣቱን  በንግድና ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ዉስጥ የተደረጉ በርካታ ውይይቶች አሳይዋል።

በመጨረሻም የግብርና ሚኒስቴር ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይህች አገር የታደለችዉን ግዙፍ ኃብት መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር አመቺ ወቅት ላይ እንዳለን እንገምታለን። ሚኒስቴሩም ባለዉ የካበተ ልምድ እና ግዙፍ መዋቅር ለዉጥ ለማምጣት ከማንም የበለጠ አቅም እንዳለው እናምናለን። ምንም እንኳን የእንስሳት እርባታ እና ግብይቱ ዘርፍ እንደማንኛዉም የምጣኔ ሃብት አካል ብዙ የተወሳሰቡ ጉዳዮች ዉጤት ቢሆንም በአንድ ጊዜ አንድ ችግር እየተቀረፈ ብዙ መፍትሄ ማምጣት ይቻላል በሚል እሳቤ ይህንን ሰነድ አዘጋጅተን አቅርበናል። ከሰነዱ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወይም ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ጋር ሆነ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሳይንሳዊ ዉይይት ለማድረግ ምን ጊዜም ዝግጁ መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ ማሳወቅ እንፈልጋለን። ይሄ ሰነድ ባለፉት በርካታ ዓመታት በተደረጉ የምርምር ስራዎች ዉጤት ላይ የተመሰረተ እና የተቻለዉን ያህል የጸሃፊዎችን የግል አመለካከት ወይም እምነት እንዳያንጸባርቅ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። ሆኖም ስህተት ሊኖር ይችላልና በዚህ ሰነድ ዉስጥ አግባብ ያልሆነ ነገር ተጽፎ ከሆነ እኛ ጸሃፊዎች ለስህተቱ ሙሉ ሃላፊነቱን እንደምንወስድ ለመግለጽ እንወዳለን።

[14] Federal Democratic Republic Of Ethiopia Central Statistical Agency Central Statistical Agency Agricultural Sample Survey Agricultural Sample Survey 2018/19 [2011 E.C.].

## Acknowledgement

This work was undertaken as part of the CGIAR Research Program on Policies, Institutions, and Markets (PIM) led by the International Food Policy Research Institute (IFPRI). PIM and Livestock CGIAR Research Programs provided funding support for this study. This synthesis is partially based on empirical findings of research projects funded by Africa RISING, International Fund for Agricultural Development (IFAD) and the International Centre for Agricultural Research for the Dry Areas (ICARDA). This paper has gone through the standard peer review procedure of ICARDA. The opinions expressed here belong to the authors, and do not necessarily reflect those of PIM, Livestock CRP, ICARDA, IFPRI, or the CGIAR.

ICARDA

Established in 1977, the International Center for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA) is a non-profit, CGIAR Research Center that focusses on delivering innovative solutions for sustainable agricultural development in the non-tropical dry areas of the developing world. We provide innovative, science-based solutions to improve the livelihoods and resilience of resource-poor smallholder farmers. We do this through strategic partnerships, linking research to development, and capacity development, and by taking into account gender equality and the role of youth in transforming the non-tropical dry areas.
**www.icarda.org**

CGIAR

CGIAR is a global research partnership for a food-secure future. CGIAR science is dedicated to reducing poverty, enhancing food and nutrition security, and improving natural resources and ecosystem services. Its research is carried out by 15 CGIAR centers in close collaboration with hundreds of partners, including national and regional research institutes, civil society organizations, academia, development organizations and the private sector.
**www.cgiar.org**